# ሰምና ወርቅ (ክፍል 1)

BY cosmos-2000

ዘርፈው ሚገደሉን በጥላቻ
የሰፈሩብን እንደ ቃልቻ
ባንዳንሆንም ስላልን ብቻ

አምና ሲዘራ ዘራ ተበድሮ
ዕዳውን ሳይከፈል በቀጠሮ
ሕግ ፊት ቀርቦ ተከራክሮ
በዘር ተቀጣ ዘንድሮ

ድፍን ሃያ ብር ሆኖባቸው
ለማከፋፈል ቸግሯቸው
ዘር ዝሩና ኑ አሏቸው

የተጣለው ጠጅ ከተጠጣ
ጮማ ስጡ አለ በቁጣ
መጋቢ ይዞት ሲወጣ
እጅ ሊነሳ እየቃጣ
ተጎነበሰ ቁርጥ ሲመጣ

ከደጃ ሰላሙ ቆመህ
ስትጸልይ ባይኔ አየሁህ
ጾሙ ስግደቱ አደከመህ
እጅ ወደ ላይ ዘርግተህ

ዛፍ ተተከለ የወይን
ተጠምቆ ጠጅ እንዲሆን
ሱዳን አለ አሉ ጥሩ ጠጅ
ወያኔ ጠጣው እጅ በጅ
ሱስ ቢይዛቸው ነው እንጅ
ሱዳን ሚሄዱ ለጠጅ
ከራስ ሲወጣ የጠጡት
ተገላበጠ መሬት

አየሩ በጣም ቀዝቃዛ
ውሃው የመጣ ከጤዛ
ስናወዛውዘው ያን ዋንዛ
ሚንጠባጠበው በዛ

ወያኔወች ሲነሱ ሊመሩ
አዋጅ አውጥተው አብራሩ
እንዲህም ብለው ተናገሩ
ለመንግሥት ስልጣን ተጋሩ